## የእድገቱ ጉዳይ
## -እድገት ከነጻነት አይለይም--

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

የቀለም ቀንድ ጥያቄ

ባለሁለት አሃዝ እድገት አለ ሲባል ዋናዎቹ መስፈርቶች ምንድን ናቸው እና እንዴት? ለምሳሌ፤ አሁንም አገራችን የአንድ ወቅት ዝናብ ሲቋረጥ ከፍተኛ ችግር መድረሱንና ለጋሾችን መለመናችንን አላቆምንም፡፡ ለመሆኑ ይህ ለብዙዎቻችን ግልጽ ሊሆን ያልቻለ ተቃርኖ እንዴት ነው የሚገለጸው? ሌሎች አገሮች ከተፈጥሮ የሚከሰት ረሃብን እንዴት ተወጡት፤ እኛስ እንዴት ልንወጣው እንችላለን? ምሳሌዎች አሉ፤ እነማን?

ዶር/ አክሎግ

በመግቢያው ላይ እንዳሳየሁት መላው የዓለም ሕዝብ የተቀበላቸው የእድገት መስፈርቶች አሉ። ከ2000 ዓ.ም. ወዲህ የተባበሩት መንግሥታት ተስማምቶ ስራ ላይ ያዋለው መስፈርት Millennium Development Goals (MDGS) በየጊዜው የሚደረጉ ለውጦችን፤ መሻሻሎችን ይገመግማል። የኢትዮጵያን እድገት በሚመለከት ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል። ለምሳሌ፤ የጀርመኑ በርቴልስማን ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር ኋላ ቀርነት ያወጣው ዘገባ እንዲህ ይላል። "ኢትዮጵያ አሁንም የዘመናዊ ኢኮኖሚ መአከል የላትም። የሚያይለው የገጠሩ ክፍል እጅግ ኋላ ቀርና ድሃ ነው። መንግሥቱ ድህነትን ለመቀነስ ያደረገው ጥረት እኛ ይህን ምርምር ባደረግንበት ወቅት መሻሻል አላሳየም።

(Government's efforts to alleviate poverty show little effect over the review period (2012)." ዘገባው የተባበሩት መንግስታት የእድገት ድርጅቶች ካወጡት አይለይም። የሚለየው፤ በፖለቲካው የብሄር ፌደራል አወቃቀርና አስተዳደር ላይ ነው። "የብሄረሰብ ፌደራል አወቃቀር ህብረተሰቡንና ሃገሪቱን በማዋሃድ በኩል ወድቋል። "Ethnic federalism has failed in resolving national integration; the opposite has happened)." ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ሕዝባዊ እቅስቃሴ እያሳየ ነው፤ በህይወቱ ዋጋ እየከፈለ ነው። በተለይ ቦኦሮምያና በአማራ ክልሎች። ኢህአዴግን የሚያሽከረክረው ህወሓት ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት አልቻለም፤ አይችልም። የችግሩን መነሻ ተቀብሎ ከሌሎች ተቀናቃይ የፖለቲካና የማህበረሰብ ድርጅቶች፤ አገር ወዳድ ግለሰቦች ጋር የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር በማድረግ ፋንታ በሁለቱም ክልሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ ወጣቶችን እያሰረ ነው። በኦሮምያ ያደረገውን አፈናና እስራት በአማራው ክልል አስፋፍቶታል። ስለዚህ፤ እንኳን ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት የግለሰቦች ህልውናም ዋስትና የለውም።

ሌላው በብዙ ማስረጃ የሚተቸው እየተባባሰ የሄደውን፤ የሃብት፤ የገቢ፤ የኑሮ፤ የስራ እድል ልዩነት ጠባብ ብሄርተኝነት፤ የከፍተኛና ጥራት ያለው ትምኅርትን ክፍተት፤ የጤና፤ የቴክኖሎጂ ስርጭት ድክመት፤ የክልል እድገት መዛባት፤ የስራ እድል አለመኖር ወዘተ ነው። በዚህ ዘገባ ድርብ አሃዝ እድገት አሳይታለች የምትባለው ኢትዮጵያ በጤና አገልግሎት ጥራት ዝቅተኛ፤ በእናቶች የወሊድ አገልግሎት ዝቅተኛ፤ በመፀዳጃ ዝቅተኛ፤ ረሃብን በመቅረፍ ዝቅተኛ፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ ዝቅተኛ ናት። እድገት ባሳየችው ከተማ በአዲስ አበባ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ዘመናዊ መፀዳጃ የለውም። ብዙ ሺህ ሕዝብ በጠለላ ይኖራል። ህጻናት ምግብ ከቆሻሻ ለቅመው ይበላሉ።

ኮንዶ ተሰርቶ ንጹህ ውሃ፤ መጸዳጃና መብራት ለማግኘት ህልም ሆኗል። ከተራ ድህነት ኃብታም የሆኑ ግለሰቦች ከውጭ ለሚሸመት መጠጥ ብዙ መቶ ዶላር ወጭ ያደርጋሉ፤ የሕዝብ ኃብት ተጠቅመው በብዙ መቶ ሽህ ዶላር የውጭ መኪና ይገዛሉ። "እንዲህ ብሎ እድገት!" የሚሉ ብዙ ናቸው።

CIA፤ ዓለም ባንክና እና ይኼ ዘገባ የተስማሙበት 39 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን

የሚያገኘው የነፍስ ወከፍ ገቢ ዓለም ባንክ ለኑሮ ያስፈልጋል ከሚለው በቀን ከሁለት የአሜሪካን ዶላር በታች፤ አብዛኛው ሕዝብ በቀን አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም ነው። የማይካደው የህወሓቷ ኢትዮጵያ ምስኪን ከሚባሉት ሃገሮች መካከል አንዷ ናት።

በዓመት የሚገመተው የነፍስ ወከፍ ገቢ $470-$480 ከሳሃራ በታች ከሚገኙ ሃገሮች አንድ ሶስተኛ ነው። ድሃው ብቻ ሳይሆን፤ ገቢያቸው ከፍተኛ ነው ተብሎ የሚነገርላቸው ኢትዮጵያዊያን፤ ለምሳሌ ፕሮፌሰሮች በኑሮ ውድነት እንደሚማረሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ስራ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የሚሰደዱበት ዋና ምክንያት የኑሮ ውድነት ነው። ሌላው የሚዘገንነው አፈና ነው።

ዩኤንዲፒና አንክታድ ባወጡት ዘገባ እንደምናየው ፈጣን እድገት ያሳየችው ኢትዮጵያ የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና የኢኮኖሚውን መዋቅር ለመለወጥ አልቻለችም። የአገር ውስጡን የግል ክፍል አፍናለች። የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙት የህወሓት ተቋሞች፤ ወዳጆችና የሚቆጣጠረው የመንግሥት ክፍሉ ናቸው። ድህንነት፤ አምባገነንነት፤ አፈና አብረው የሚሄባት አገር ሆናለች። ድሃዋና ኋላ ቀሯ ኢትዮጵያ ጥቂት በኪራይ ሰብሳቢነት የከበሩ ሚሊየኔሮችን አምርታለች። ባለፉት ወራቶች በተከታታይ የሚታየው ሃቅ አንድ ነው። ሕዝቡ መንግሥቱን ንቆታል፤ ነጻነት፤ ነጻነት ይላል፤ ህወሓቶችና የፈጠራቸው ቃብታሞች ያለው እንዲቀጥል ይፈልጋሉ።

መንገዶች፤ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች፤ ቪላዎች፤ ሃዲዶች፤ ግድቦች፤ ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ ኮሌጆች ተሰርተዋል። ሆኖም፤ የአየር ሁኔታ እንዳሁኑ ሲለወጥ ከ15-20 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ይራባል፤ አገሪቱ እርዳታ ትለምናለች። ይህ የእድገት እንቆቅልሽ እንዴት ሊከሰተ ቻለ፤ እንዴት እድገቱን ከድህነቱና ከረሃቡ ጋር እናስታርቀው? የሚለው ጥያቄ ቁልፍ ነው። እኔ ይኼን ሁኔታ "ልማታዊውን መንግሥት" በመተቸት፤ የሚከሰተውን አደጋ በሶስት መጻህፍት በመራጃዎች በመተንተን የፖለቲካ ኢኮኖሚ አመራር ለውጥ እንዲደረግ አሳስቤ ነበር--

Waves: endemic poverty that globalization can't tackle but Ethiopians can (2010), Ethiopia: the great land giveaway, 2011 and ድርጅታዊ ምዝበራ, 2014. እነዚህ መጻህፍት በኢትዮጵያ ታትመው ለወጣቱ ትውልድ ቢሰራጩ ይጠቅማሉ የሚል እምነት አለኝ።

የሚጠቅሙበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያን እድገት ከሌሎች አገሮች ጋር በማነጻጸር አማራጮችን ስለሚያቀርቡ ነው። በተከታታይ የሚታየው ችግር ገዢው ፓርቲ የሌሎችን ሃሳብና ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኖ አያውቅም። የሚፈልገውና የሚመካው "እሽ፤ ምን ልታዘዝ" በሚሉ ካድሪዎች ብቻ ነው። አንድ ቻይኒስ የራሱን መንግሥት ሲተች እንዲህ ይላል። "ከአንድ ሺህ እሺ ጌታየ ምን ልታዘዝ ከሚሉ አገልጋዮች አንድ እውነቱን የሚናገር አማካሪ ይበልጣል።"

በአማራው ክልል እንደታየው ህወሓት የሚጠቀመው የክልሉን ነዋሪ በማባበል፤ በማስፈራራትና በመደለል ነው። ከህወሓት በላይ ህወሓቶች የሆኑ አማራዎች፤ ኦሮሞዎች ይታያሉ። ህወሓት ሁልጊዜም ቢሆን ስህተቶችን በስህተቶች ለማሻሻል ስለሚሞክር እነዚህ ከሕዝብ ጥቅም በላይ ለራሳቸው ጥቅም የቆሙ ግለሰቦችና ስብስቦች ሁኔታውን አባብሰውታል። ከውስጡ ይኼ ስራ አደገኛ ነው የሚል ደፋር ግለሰብ ወይንም ቡድን የለም።

ወደ መሰፈርቱ ልመለስና MDGS ትኩረት ከሰጣቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ ድህነትን መቅረፍ ነው። በዚህ መስፈርት ኢትዮጵያ ፍጹም ድህነት ከበፊቱ ጋር ሲነጻጸር ቀንሳለች የሚለውን እቀበላለሁ። መሰረተ ልማት ተስፋፍቷል፤ ሲስፋፋ ዜጎችም የተሻለ ኑሮ ይኖራሉ። የድህነቱ መቀነስ አሃዝ አከራካሪ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ቦታወች የገቢ መጠን ጨምሯል።

ለምሳሌ የጥቂት ገበሬዎች፤ የነጋዴዎች፤ የዝቅተኛ አምራቾችና አገልግሎት ሰጭዎች ለውጥ አሳይተዋል። ሆኖም፤ ከአብዛኛው እየጨመረ ከሄደው ሕዝብ የኑሮ መሻሻል አንጻር ሲታይ አሁንም አሰቃቂ ድህነትና ረሃብ ይታያል። ኢትዮጵያዊያንና እንደኔ ያሉ የኢትዮጵያ ትውልድ ያላቸውን ምሁራን ትችት ወደጎን ትተን እውቅና ያላቸውን የውጭ ድርጅቶችና ሊቃውንት ዘገባ ማየቱ ሚዛናዊ ይሆናል።

ማንም አገር የውጭ ኢንቬስተሮችን ቃብዞና ተማምኖ አገር ተከል የሆነ፤ ራሱን የቻለ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ለመመስረት አይችልም። UNCTAD, Most of the World's poorest nations stuck in a structural rut," December 2014 የሚነግረን ኢትዮጵያ አሮንቃ ከገቡትና ድህነት መዋቅራዊ ከሆነባቸው ሃገሮች

መካከል አንዷ መሆኗን ነው።

“The planet’s poorest nations, like Ethiopia, Malawi and Angola have failed to cash in on strong economic growth due to a lack of structural reforms that left them wallowing in poverty,” said AFP quoting UNCTAD. “The LDC paradox (እንቆቅልሽ) arises from the failure of LDC economies to achieve structural changes despite having grown vigorously as a result of strong export prices (Angola), and rising aid flows (Ethiopia)...እንደ ኢትዮጵያ፤ ማላዊ እና አንጎላ ያሉት ድሃ አገሮች ፈጣን እድገት ቢያሳዩም ለድህነት መሰረት የሆነውን የፖሊሲና የመዋቅር መሰናክሎች ለመቅረፍ አልቻሉም... የእድገታቸውን መጠን ተጠቅመው ዘላቂነትና ፍትሃዊነት የሚያሳይ የእድገት መሰረት አልጣሉም።” ጥናቱ የኢትዮጵያ ፈጣን እድገት የውጭ እርዳታ ውጤት መሆኑን ያረጋግጣል።

በአሁኑ ወቅት የውጭ ምንዛሬ እጥረት ስላለ መንግሥት በገፍ ይበደራል፤ ብድሩ አስተማማኝ ከሆነ ፕሮጀክት ላይ አይውልም፤ ይባክናል፤ ይሰረቃል የሚሉ ብዙ ናቸው። የምስራቅ ኤዢያ፤ የቬትናም፤ የቻይና፤ የቦትስዋና፤ የሩዋንዳና ሌሎች ፈጣን እድገት ያሳዩ አገሮች ታሪክ እንደሚያሳየን የውጭ እርዳታ፤ ብድር፤ ድጎማ፤ ኢንቬስትመንት ሆነ በውጭ ንግድ የሚገኝ ገቢ ብቻውን ድህነትን አያጠፋም። እዳ መሸከም ችግሩን ያባብሰዋል እንጅ አይፈታውም። ማነቆ የሆነውን መዋቅር ለመለወጥ የፖሊሲውንና የኢንቬስትመንቱን ትኩረት መለወጥ ያስፈልጋል። የፖሊሲውን ለውጥ ስኬታማ ለማድረግ የመንግሥት ሃላፊዎች ፈቃደኛነት ወሳኝ ነው።

የሕዝቡ ድምጽ መሰማት አለበት፤ ግልጽነት መኖር አለበት፤ ሙስናና የጎሳ አድልዎ መቀረፍ አለበት። የፖለቲካው አመራር አሳታፊና ዲሞክራሳዊ ካልሆነ አሁን ያለው የድህነትና የረሃብ “አዙሪት” (Vicious cycle) ይቀጥላል።

እዚህ ላይ ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ የተናገሩት ትዝ ይለኛል። “ልማት የፈለገ ሕዝብ በጥቂት “ቀላዋጮች” ወደኋላ መጎተት የለበትም። በተመሳሳይ፤ ለልማት የተሻሻለ መንገድ እፈልጋለሁ የሚል ሕዝብ እጣውን ለጥቂት ሰዎች በአደራ አያስረክብም።” ለነጻነቱና ለመብቱ መታገልና መስዋእት መክፍለ አለበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋእት እየከፈለ ነው። ይህን ብሂል በማስረጃ ልግለጸው።

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ምሰሶዎች ባለቤት ማነው?

ኢትዮጵያ ምርትና የስራ እድል ሳትጨምር ከችግሯ ላይ ችግር እየጨመረች ነው። እድገቷን ስኬታማ ለማድረግ በአብዛኛው የምትመካው በውጭ ብድር፤ በውጭ ኢንቬስትመንት፤ በውጭ እርዳታ፤ ስደተኛው በሚልከው በውጭ ምንዛሬ፤ ቦንድ በመሸጥና በአገር ውስጥ ብድር ነው። ብር በገፍ የሚመረት ይመስላል። ገዢው ፓርቲ በውጭ እርዳታና ብድር የሚመካበት ዋና ምክንያት አገሪቱ በአማካይ ወደ ውጭ የምትልከው እቃ የሚያስገኘው በአመት $3 ቢሊየን ብቻ በመሆኑ፤ ከውጭ የምትሸምተው እቃ ወጭ ከ$10-$13 ቢሊየን በመሆኑ ነው። ባለፈው ዓመት የተከሰተውን የ$10 ቢሊየን ክፍተት፤ ጉድለት እንዴት ለማሟላት ይቻላል? በሚከፈል ብድር።

ቻይናዎች ለማበደር ችሎታ አላቸው፤ ፈቃደኛነት ያሳያሉ፤ ጥቅማቸውን ያውቃሉ። የኢትዮጵያ ግዙፍ መሰረተ ልማት---መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ሃዲዶች፤ ታላላቅ ግድቦች፤ የአየር ማረፊያዎች፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ወዘተ የሚሰሩት በቻይና ብድርና ሰራተኞች አመራር ነው የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። ቻይና ለኢትዮጵያ መሰረተ ልማት $17 ቢሊየን አበድራለች። ተርኪ በኢትዮጵያ ከሚንቀሳቀሱ አስር የውጭ ኢንቬስተር (Foreign Direct Investment) አገሮች መካከል ከፍተኛ ደረጃ የያዘች ናት። ይህች አገር $3 ቢሊየን አበድራለች። ህንድ በመሬት ነጠቃና ቅርሚት ተካፋይና ለገዢው ፓርቲ ባለውለታ ናት፤ $1 ቢሊየን አበድራለች።

ዓለም ባንክ መንግሥት ካልሆኑ አበዳሪዎችና ለጋሶች መካከል ከፍተኛውን ደረጃ ይዟል፤ እስካሁን ያበደረው $6 ቢሊየን ነው። በተጨማሪ ኢትዮጵያ $1.5 ቢሊየን ዩሮ ቦንድ ገዝታለች፤ መክፈል አለበት። የታወቀውን መሰረት አድርገን ስንደምረው፤ የአገሪቱ የውጭ እዳ $28.5 ቢሊየን በላይ ደርሷል። የኢትዮጵያን ሕዝብ አመኔታ ካላስገኘውና አከራካሪ ከሆነው $54 ቢሊየን ጠቅላላ ገቢዋ ከአምሳ በመቶ በላይ

መሆኑ ነው። ልክ በምስራቅ ኤዢያና ፓሲፊክ፤ በላቲን አሜሪካ እንደሆነው አበዳሪዎች ብድሬን ክፈሉኝ ሲሉ እንዴት ይከፈላል? ብለን መጠየቅ ብሄራዊ ግዴታችን ነው። ቱርኮችን፤ ቻይኒሶችን ሊለመን ነው?
ብድሩ ካልተከፈለ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ይከስራል፤ ይወድቃል።

አንድ ሚሊየን የሚያወጣ ቤት ግማሽ ሊሆን ይችላል። መለዋወጫ መሳሪያ ከውጭ ለመሸመት አይቻልም። መኪና በብድር የገዛ ግለሰብ መኪናው ይወረሳል ወዘተ። የኔ ብጤው መጨነቅ የለበትም። ኃብት ያለውና የተበደረው፤ አገሪቱን ጨምሮ መጨነቅ አለባቸው። ዓለም ባንክ ብድርን በሚመለከት የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚችለው በላይ የሚበደር መሆኑን አስጠንቅቆ ነበር። ብድሩ ባይከፈል ምን ይሆናል? አለመክፈል አማራጭ አይሆንም። ሌላ ዘዴ ካልተገኘ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወይንም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይንም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ወይንም ሁሉም መሸጥ ይኖርበታል። ከብድሩ ጥቅም ያላገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ እዳውን ከፍሎ የራሱን ኃብትና ብሄራዊ ተቋሞች ያጣል ማለት ነው።

ሁለተኛውና የባሰው ችግር የዘመናዊ እንዱስትሪዎች በውጭ ኢንቬስተሮች ባለቤትነት መያዛቸው ነው። ኢትዮጵያ 51 በመቶ ኢትዮጵያዊ፤ 49 በመቶ የውጭ ኢንቬስተሮች የሚል ልምድ አላት። እንደምትታለብ ላም ራሷን አጋልጣ ለውጭ ኢንቬስተሮችና ለጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎች አመቻች የሆነችበት ወቅት በአሁኑ መንግሥት ነው። ራሷንም አጋልጣ የምታገኘው ጥቅም በጣም ዝቅተኛ ነው።

አገር ወዳድ አመራር ባላቸው አገሮች የውጭ መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ የሚፈለገው ቴክኖሎጂን በፍጥነት ለማሰራጨትና አገር ተከል ለማድረግ፤ ብዙ ሚሊየን የስራ እድል ለመፍጠር፤ ምርቶችን ለአገር ውስጥና ለውጭ ፍጆት ለማቅረብ፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት መሰረት በመጣል የመካከለኛውን መደብ ለማሳደግ ነው። ኢትዮጵያ በያመቱ 2,000,000 የስራ እድል መፍጠር አለባት።

በዚህ መስፈርት ብቻ ብናየው ኢንቬስተሮች ያመጡት ጥቅም ያሳፍራል። ከ2011/2012 አስር አገሮች--ተርኪ፤ ኢንድያ፤ እንግሊዝ፤ ሰሜን ሱዳን፤ ቻይና፤ ካታር፤ አሜሪካ፤ ጀርመኒ፤ ኢታሊና ሆላንድ 60.5 ቢሊየን ብር ፈሰስ አድርገዋል። ሰባ አንድ (70) በመቶ የሚሆነው ኢንቬስትመንት ለጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ምርት፤ አበባ አምርቶ ለውጭ ገበያ ለማቅረብና ተመሳሳይ ነው። ጠለቅ ብየ ስመራመረው የኢትዮጵያ የውጭ መዋእለንዋይ ፈሰስ የሚያስታውሰኝ "የሙዝ ሪፐብሊክ፤ Banana Republic" ተብለው የሚጠሩ የካሪቢያንና የመካከለኛው ላቲን አሜሪካ አገሮችን ሁኔታ ነው።

እነዚህ አገሮች በአሜርካ ኩባንያዎችና በአገሮቻቸው ኪራይ ሰብሳቢዎች ተባባሪነት ስለተማረኩ "ነጻነታቸውና ሉዐላዊነታቸው" ወድሞ ነበር። የሚከፈለው ደሞዝ ዝቅተኛ ነበር። ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ የተራራቀ አይደለም። ቻይኒሶች 93 ኩባንያዎች አሰማርተዋል፤ 69,000 ሰራተኞች በዝቅተኛ ደሞዝ ቀጥረዋል። የቴክኖሎጅ ስርጭት የሚባል ነገር የለም። ቱርኮች ኢትዮጵያን የወረሯት ይመስላል፤ 341 ኩባንያዎች አሰራጭተው 50,000 ኢትዮጵያዊያንን በዝቅተኛ ደሞዝ ቀጥረዋል።

አሜሪካኖች $4 ቢሊየን ፈሰስ አድርገዋል፤ ብዙ ኩባንያዎችን አሰራጭተዋል። ተመልካቾች የመጀመሪያውን የኢንቬስትመንት ደረጃ ይዘዋል ይላሉ። ለስንት ኢትዮጵያዊያን የስራ እድል እንደፈጠሩና ምን ያህል የቴክኖሎጂ ስርጭት ስኬታማ እንዳደረጉ አይታወቅም። አሜሪካኖች ከሌሎች ይሻላሉ ለማለት መረጃ የለም። ሁሉም ኢንቬስተሮች የሚሰሩት ለራሳቸው ትርፍና ጥቅም ነው። ለማጠቃለል፤ እነዚህ የውጭ ኢንቬስተሮች ያፈሰሱት መዋእለንዋይ ለኪራይ ሰብሳቢዎች ከፍተኛ ገቢና የድሎት ኑሮ ከማስገኛቸው ባሻገር ከላይ ያቀርብኳቸውን መስፈርት አላሟሉም። እንዲያውም የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት በክለውታል።

ሆላንድ ቲንሽ የነጋዴዎች አገር ናት። ደቾች በኢትዮጵያ ፈሰስ የማድረግ ልምድ አላቸው። በአለፉት አስር ዓመታት በኢትዮጵያ 130 ኩባንያዎች እንዳሰራጩ የራሳቸው መንግሥት ጠቅሷል። ከተሰማሩባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል፤ የሃይንከን ቢራ ፋብሪካ ከፍተኛውን ቦታ ይዟል። ለማስታወስ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕዝብ የነበሩትን የቢራ ፋብሪካዎች በዝቅተኛ ዋጋ ሸጧል።

ከእነዚህ መካከል እውቅና የነበራቸው የበደሌና የሃረር ቢራ ፋብሪካዎች ይገኙበታል። እነዚህና ሌሎች ብዙ ሽህ ቤተሰቦችን ይደግፉ ነበር። የበደሌ ቢራ በዓመት 1.5 ቢሊየን ዩሮ ግብር ይከፍል ነበር። የሃረር ቢራ በዓመት አንድ ሚሊየን ዩሮ ግብር ይከፍል ነበር። ለማመን የሚያስቸግረው፤ ሃይንከን በዓመት የሚከፍለው 900,000 ዩሮ ብቻ ነው። ትርፉ ይጭበረበራል ማለት ነው። አንድ መንግሥት በሕዝብ ባለቤትነት ተይዞ ትርፍ

የሚያስገኝ ተቋም ሽጦ ዝቅተኛ የሚያስገኝ የውጭ ተቋም ሲተካ ህወሓት የመጀመሪያው መሆኑ ነው። በደሌና ሃረር ቢራ ሲሸጡ የሰራተኛው ቁጥር በ700 (44 %) ቀንሷል።

የሆላንድና የኢትዮጵያ መንግሥታት ሃይንከን የስራ እድል ፈጠረ የሚሉት "በሬ ወለደ" ከሚለው አይሻልም። ከግብር ማጭበርበር ሌላ፤ ከላይ የተጠቀሱት የደች ኩባንያዎች ኢትዮጵያዊያንን ቦታ ለማሳጣት የሚያስችል የሆላንድ መንግሥት ድጎማ ያገኛሉ። ለምሳሌ፤ ሃይንከን በዓመት 1.5 ሚሊየን ዩሮ ድጎማ ይሰጠዋል፤ ማንም ኢትዮጵያዊ ኩባንያ ሊወዳደር አይችልም።

በተጨማሪ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የራሱን ዜጎች ከመሬታቸው አስወግዶ ለደቾችና ሌሎች መሬት አስረክቧል። ዜምብላ የተባለው የሆላንድ ተቋም ጋዜጠኞች ልኡካን በኢትዮጵያ ያለውን የሕዝብ ተቃውሞ ለመመራመር ሄደው የተሰጣቸው የሕዝብ ተቃውሞ እንዲህ የሚል ነው። "መንግሥታችን መሬታችን ቀምቶ ለነጮች ሰጠብን…እኛን ለመከፋፈል ሞከረ…።

" ልማቱን ለምን አወደማችሁ? የሚል ጥያቄ ተነስቶ እንዲህ ብለዋል። "ከአምባገነን መንግሥት ጋር ተሻርኮ ከመስራት ይልቅ የአካባቢው ነዋሪዎች ሊጠቀሙ በሚችሉበት መንገድ መስራት ይቻላል…ይህ ካልሆነ ግን ማውደሙን እንቀጥልበታለን።" ሌብነት በምስጢር የሚሰራው ሽርከኛ ሲኖር ነው። የመንግሥት ኪራይ ሰብሳቢዎች የአገሪቱንና የሕዝቡን ጥቅም በራሳቸው የግል ጥቅም ቀይረውታል። በእድገት ስም፤ "ጥቂት ቀላዋጮች" ሃላፊነት በጎደለው መልክ የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት አዘቅት እያስገቡት ነው። ለዚህ ነው፤ ሕዝብ በመንግሥት ላይ እምነት የሌለው። ለዚህ ነው ሕዝብ ለህይወቱ ሳይፈራ-- ከትግራይ ክልል ውጭ-- በመላው ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመጽ የሚካሂደው። ሕዝብ በመንግሥት ላይ ምንም እምነት እንደሌለው በተደጋጋሚ ሕዝባዊት እይንቶች ታይቷል።

ሕዝብ በመንግሥቱ ላይ እምነት የሚኖረው መንግሥት ለራሱ ተጠሪና አገልጋይ ሲሆን ነው። "ቀላዋጮች" ለሕዝብ ደንታ የላቸውም። ህወሓቶ ይሉኝታ የሚባል ነገር በባህላቸው የለም። ይልኙታን፤ ትእግስትን፤ መቻልንና መቻቻልን እንደድክመት ያዩታል። ደንታ ከሌላቸው ሕዝብ የራሱንና የልጆቹን እድል "ለጥቂት ሰዎች በአደራ" ማስረከብ የለበትም። አላስረክብም ብሎ የሚሞተው ለዚህ ነው። ሕዝቡ የፖለቲካ ድርጅቶችንና ልሂቃን/ምሁራንን ቀድሞ ሄዷል ለማለት እንችላለን።

የተቀናቃኙ ክፍል ልዩነቶቹን ወደጎን ትቶ ከሕዝብ ጎን ከቆመ ይከበራል፤ ፈርቶና ተከፋፍሎ ወደጎን ካፈገፈገ ዋጋ ቢስ ይሆናል። ተገቢውን ቦታ ለህወሓቶችና ለሰርጎ ገቦች ካስረከበ የሚፈርደው በራሱ ላይ ነው። ከአገዛዙ አንጻር ስመረምረው የተሰበረን ጠርሙስ በሙጫ ለመጠገን አይቻልም። በተመሳሳይ ስር የሰደደን ድህነት ገንዘብ በማተም፤ በመበደር፤ የብርን ዋጋ በመለወጥ፤ ወጣቱን በመግደልና በማሰር ማሻሻል አይቻልም። ግድያና አፋና እንዲያውም ሁኔታውን ያባብሰዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ኑሮ በተከታታይ የብር ዋጋ መቀነስና የዋጋ ግሽበት ተበክሎ የመግዛት አቅሙን አድክሞታል።

የአሁኑ መንግሥት ስልጣን እንደያዘ የብር ዋጋን 59 በሙቶ ቀንሷል። የሰጠው ምክንያት ወደ ውጭ የሚላከው ጥሬ እቃ እንዲያድግና በዓለም ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚል ነው። የትኛው ጥሬ እቃና ከማን ጋር? ብለን ስንጠይቅ አጥጋቢ መልስ አናገኝም። ከዚያ ወዲህ የብር ጥቅም በተከታታይ ቀንሷል። አንድ ዶላር 9.6 ብር (2008)፤ 11.8 ብር (2009)፤ 14.4 ብር (2010)፤ 16.9 ብር (2011)፤ 17.8 ብር (2012) እና 20 ብር (2014)። የማይቆም ባቡር ይመስላል።

የኢትዮጵያን የዋጋ ግሽበት በትክክል ለማወቅ አይቻልም። በ2011 መንግሥት ባወጣው ዘገባ 30 በሙቶ የነበረው በ2012 ወደ 22 በሙቶ ወርዷል። የብር ጥቅም መውረዱንና የዋጋ ግሽበት ወደ ሰማይ መወርወሩን ለማወቅ የሚቻለው ተራው ዜጋ ከሚከፍለው ዋጋና ከሚኖረው አሰቃቂ ኑሮ አንጻር ብቻ ነው። መንግሥት ከሚሰጥው መረጃ አንጻር አይደለም። የእድገቱ ኢኮኖሚ ለብር ዋጋ መናድ፤ ለኑሮ ውድነትና ጥልቀት ላለው ድህነት ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል። መረጃው የሚያሳየው በደርግ መንግሥት ከ1974-1990 ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሃገሮች ዝቅተኛ የዋጋ ግሽበት ነበራት፤ በልቶ ማደር ብርቅ አልነበረም።

ዛሬ ብዙ ገንዘብ እየተዘዋወረ ጥቂት አቅርቦትን ይሻማል። ያለው ይበላል፤ የሌለው ጦሙን ያድራል። አንድ ግርሻ ብርቅ ሆኗል። ያላቸው ጥቂት ኃብታሞች የሚነዱት መኪና፤ የሚጠጡት ልዩ ከውጭ የሚሸመት

መጠጥ፤ የሚበሉት ልዩ ምግብ፤ የሚኖሩበት ምርጥ ቤት ወዘተ ተደማምሮ ሲታይ በድሃው ሰፊ ሕዝብ ላይ አሰቃቂ ሁኔታ እንደተፈጠረ ሊካድ አይችልም።

አቅርቦት ከፍላጎት ጋር አልተመጣጠነም፤ አቅርቦትም ሲኖር የዋጋ ግሽበት አልቆመም። የመግዛት አቅም የለም፤ የመግዛት አቅም ያለው የፖለቲካ ስልጣን የሚጠቀመው ኪራይ ሰብሳቢ ነው ለማለት እንችላለን። በእርሻ ምርት ውጤት መስፈርት ስናይ፤ የኬንያ ዝቅተኛ አምራቾች የኢትዮጵያን በእጥፍ ይበልጣሉ፤ የደቡብ አፍሪካ ከኢትዮጵያ አስራ ስድስት ጊዜ ይበልጣል። ችግሩን መቀበል መፍትሄዎችን ለመፈለግ ያስችላል ቢባልም፤ የህወሓት መንግሥት ችግሩን የተቀበለበት ጊዜ ፈልጎ ለማግኘት አይቻልም። በምድር ላይ ያለውን የኑሮ ሁኔታ ቅንነትም ቢኖር መካድ አይቻልም። የህወሓት መንግሥት ችግሩን በመካድ መፍትሄ የሚያገኝ ይመስለዋል። በእኔ ግምት ችግሩን ለመፍታት አይቻልም።

ሕዝቡ ከሰሜን ጎንደር እስከ ሞያሌ ለነጻነቱና ለሙብቱ የተነሳበት መሰረታዊ ምክንያት የእድገቱ ቋሚ ተመላካች እንጅ ተጠቃሚ ባለመሆኑ ነው። “የድርብ አሃዝ እድገት” ትርጉም የለሽነቱን የሚተቸው ሕዝቡ መሆኑን አለመቀበል አደጋውን ማባባስ ነው።

***http://www.ethiopanorama.com***